# የጋሞ ጎፋ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ

# የ2002 ዓ.ም ዕቅድ

ሰኔ 2001

አ/ምንጭ

1. መግቢያ

በአገራችን ብሎም በክልላችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ከልማቱም ህዝቡን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ እንዲቻል መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም የመገንባት ሥራ ትኩረት በመስጠት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ / BPR / በክልላችን ሙሉ በሙሉ በመተግበር ተቋማዊ ለውጥ/ Organizational Transformation / የማምጣት ጉዳይ ትኩረት ይደረግበታል፡፡

በመሆኑም የዞናችን ሕዝብ ከሚገኝበት ኋላ ቀርነትና ድህነት እንዲላቀቅ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገብናቸውን የልማት ውጤቶች ዘላቂ እንዲሆኑና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በዞናችን የሚታዩ የማስፈጸም አቅም ችግሮችን ሊፈታ የሚችል የዳበረ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር መግባት ይጠይቃል፡፡

በየደረጃው የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመፍታት ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከር፣የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ፈጥኖ መፍታት የሚያስችል ስልት በመቀየስ በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግና አጠቃላይ የሪፎረም ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ በማስተገብር በመንግስት ተቋማት ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንዲቻል መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ማድረግና የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት መዘርጋት ቁልፍ የትኩረት መስክ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ በዋናነት የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስርዓት ማስፈን፤ በመንግሥት ተቋማት ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራርን መዘርጋት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአቅም ግንባታ መምሪያ ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸውን ተግባራትንና ያጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም የተገኙ ውጤቶች፤ ክልላዊ የትኩረት አቀጣጫዎችንና የሴክተሩ

ስትራቴጂያዊ ግቦች በዋና ግብዓትነት በመውሰድ የ 2002 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. ያለፈው በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር ግምገማ

በክልላችን የተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ጥናት ከሙከራ ትግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ ሽግግር ሲደረግ በድልድል ደንቡ እና በማስፈፀሚያ እስራቴጂው ላይ ከ20 ዞንና ዞናዊ ባህርይ ላላቸው መምሪያዎች ፣ ለ15ወረዳ ጽ/ቤቶች እና በ2ቱ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ፈፃሚዎች ለአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቶ ግንዛቤ በማስጨበጥ ወደ ድልድሉ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ፈፃሚው በድልድል ደንቡ ፣ በጥናት ሰነዱ በሚጋብዘው የሙያ መስመር ፣ በትምህርት ዝግጅት እንዲሁም አግባብ ባለው የሥራ ልምድ አሟልተው ስለመደልደላቸው በየሴክተሮች ተገኝቶ በማጣራት የተጠናቀረ መረጃ ለክልሉ አ/ግ/ቢሮ እና ለዞኑ ስትሪንግ ኮሚቴ የተላለፈ ሲሆን በአፈፃፀም በታዩ ክፍተቶችም ድጋፍ ተሰጥቷል ፡፡

በተመረጡ በዞን 7 ሴክተሮች ፣ በ15 ወረዳ እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ሠራተኛው በጥናት ሰነዱ በተቀመጠው እስታንዳርድ መሠረት እቅዱን በመፈፀም ጥናቱን መሬት በማስረገጥ ለውጡን በተቋማት እንደስርአት መትከል ይቻል ዘንድ በየተቋማቱ በ15 ቀን ለአንድ ቀን ከ2:00 ሰዓት በላይ ድጋፍ እና ክትትል ተደርጓል፡፡

በሌላ መልኩ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡን ተቋማዊ መልክ ለማስያዝ በወረዳ ለሚገኙ ጽ/ቤቶች በተቀመጡ በጥረት ተደራሽ ግቦች ፣ ከሚጠበቁ ውጤቶች እና እስታንዳርድ መሠረት እንዲፈፀም ድጋፌዊ ክትትል ተደርጐ በአፈፃፀም መሻሻል ታይቷል ፡፡ ከዚህ ባሻገር የአመለካከት እና የአፈፃፀም ለውጥ ለማምጣት የሠራተኛውን ግንዛቤ በማሣደግ የለውጥ ኃይሎችን ለማበራከት ለ500 ሰራተኞች አጫጭር ስልጠና በመስጠት የፈፃሚውን አቅም ለማብቃት ተችሏል ፡፡

የመልካም አስተዳደር ፖኬጁን ተግባራዊ ለማድረግ ፈጻሚዎች በእውቀት ሥራውን ማከናወን እንዲችሉ የእቅድ እንስፔክሽን እና ሱፐርቪዥን አደረጃጀት እና አሠራር ማስፈጸሚያ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለ15ቱ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በማሠራጨት ፣ በአፈፃፀሙ ግንዛቤ በመፍጠር ፣ ድጋፍ እና ክትትል ተደርጓል፡፡

ህብረተሰቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሳተፍና አሳምኖ የማሰራት ባህልን በማዳበር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሠራርን በመዘርጋት በህዝቡ ተሰትፎ እቅድ የማዘጋጀት እና

ሞዴል አመራረጥ እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፋፋት አፈፃፀምን በሚመለከት ፤

የተቋሙን እቅድ ስኬታማና ውጤታማ ለማድረግ ከ15ቱ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት እና ከ2ቱ ከተማ አስተዳደር ለተውጣጡ አመራሮች እና ባለሙያዎች በእቅድ ዝግጅት እና አፈፃፀም ፎረም ተዘጋጅቶ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ ህብረተሰቡ ያመነበትን ሥራ በራሱ ተነሳሽነት የተለያዩ የልማት እቅዶችን አቀናጅቶ ወደ ሥራ እንዲገባ የእቅድ አዘገጃጀት ንድፈ ሀሣብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ማኑዋል እንዲሁም የሞዴል መንደርና አርሶ አደር መምረጫ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለ15ቱ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በማሠራጨት የማስፈፀሚያ አቅምን የማጐልበት ሥራዎች በመስራት እና በአካል በወረዳዎች በመገኘት ድጋፍ ተደርጓል፡፤

የፍትህ አካላቱን / ፍርድ ቤት ፣ ፖሊስ ፣ አቃቤ ህግ እና ማረሚያ ቤቶች/ የማስፈፀም አቅም ለማጐልበት ፣ ከ15ቱ ወረዳ እና ከ2ቱ ከ/አስተዳደር በተውጣጡ ፍትህ አካላት መካከል ፎረም በማዘጋጀት በፍትህ ሥርዓት አገልግሎት አሰጣጡ ውይይት በማካሄድ እና የልምድ ልውውጥ በማካሄድ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል ፡፡ በሌላ መልኩ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ በየፍትህ ሴክተሩ በ15 ቀን አንድ ጊዜ በመገኘት ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር በወር አንድ ቀን የጋራ መድረክ በማዘጋጀት የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲጐለብት የተደረገ ሲሆን በህብረተሰቡ ተሣትፎ ወንጀልን ከሥሩ ለማድረቅ የተቀናጀ እቅድ በመዘርጋት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ማስፈፅሚያ መመሪያ ለዞን ፍትህ ሴክተሮች ፣ ለ15ቱ ወረዳ እና ለ2ቱ ከተማ አስተዳደር አቅም ግንባታ እና ፍትህ ሴክተሮች ከመሠራጨቱም በላይ የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ ፣ የፍትህ አካላት ፣ የሐይማኖት ተቋማት ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ ክፍለ - ከተማዎች ፣ ቀበሌያት እና ታዋቂ ግለሰቦችን ያሣተፈ ውይይት በማካሄድ ከዞን እስከ ቀበሌ የሚያገለግል እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ተጠናቆ ወደ ትግባራ ያልገቡ እና ጥናታቸው ተጠናቅቆ ወደ ትግበራ የገቡ ሴክተሮችን በሁለት በመክፈል የአፈፃፀም እቅድ እና አጀንዳዎችን እንዳሉበት ሁኔታ ለይቶ በማዘጋጀት በየሴክተሩ በ15 ቀን አንድ ጊዜ ለሁለት ሰዓት ጥናት ባልተጠናቀቀባቸው በአገልግሎት አሰጣጡና በሪፎርም አፈፃፀም እንዲሁም ጥናት በተጠናቀቀበቸው በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት አፈፃፀም ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን በወር አንድ ቀን በአቅም ግንባታ የለ/ኘ/የኘ/ጥ/ት/የሥራ ሂደት ሰብሣቢነት ጥናት ባልተጠናቀቀባቸው የየሴክተሩ የሪፎርም አካላት ጥናቱ በተጠናቀቀባቸው የሂደት አስባባሪዎች የጋራ መድረክ በመፍጠር በየተቋሙ ያልተፈቱ

ለአገልግሎት አሰጣጡ አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮች ወደ ጋራ መድረኩ እየቀረቡ የሚፈቱ ሲሆን የልምድ ልውውጥም በተደረገው የአመለካከት ለውጥ መጥቷል ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ቀደም ሲል ከነበረበት መሻሻል አሳይቷል፡፡

በሌላ በኩል ወደ ትግበራ ባልገቡ ሴክተሮች የአገልግሎት አሰጣጡ እና የሪፎርም አፈፃፀም ያለበትን ደረጃ ለመለየት የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ለሚመለከተው ክፍል የተላለፈ ሲሆን በታየው ክፍተትም ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

*ጤናማና ምርታማ ዜጋ ከማፍራት አኳያ በሥርዓት ጾታና ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ሜይንስትሪሚንግ በተቋሙ በማድረግ የተመዘገቡ ውጤቶችን በሚመለከት ፣*

መምሪያችን የፈፃሚውን ግንዛቤ በማሳደግ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣ በየወሩ አንድ ቀን በሠራተኛው መካከል ውይይት በማካሄድ ፣ መልእክት አስተላላፊ ፖስተሮችን ሠራተኛው አዘውትሮ በሚገኝበት ቦታ በመለጠፍ እንዲሁም በራሪ ወረቀቶችን በማሠራጨት የሠራተኛው ግንዛቤ እንዲጐለብት የተደረገ ሲሆን ለዚሁም ሥራ ማስኬጃ እንዲሆን ከተቋሙ በጀት ላይ 2% በማስመደብ ለዚሁ አገልግሎት በማዋል አጠቃላይ የሠራተኛ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ በመፈጠሩ በተለያዩ አርዕስቶች ላይ በመወያየት እና ውሣኔዎችን በማሳለፍ ተንቀሳቅሷል፡፡ በዚህ ዓመትም በ224 ተሳታፊዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለመስራት ታቅዶ ይህ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን 6 መልዕክት አዘል ብሮሽሮች እንዲሁም ወረርሽኙን በሥራ ላይ መከላከልና መቆጣጠር መመሪያ ለ20 ዞንና ዞናዊ ባህሪይ ላላቸው መምሪያዎች ለ15ቱ ወረዳ ጽ/ቤቶች እና ለ2ቱ ከተማ አስ/አግ/ጽ/ቤቶች ተላልፎ በሥራ ላይ ውሏል ፡፡

የሴቶችን ተሣትፎ በማሳደግ የአፈፃፀም ብቃት ከማጐልበት አኳያ በተያዩ ስልጠናዎች ፣ ወርክ ሾፖች እና ስብሰባዎች እንዲሣተፉ የተደረገ ሲሆን በተቋማችን በተለያዩ ኮሚቴ አባልነት በማሳተፍ የሴቶች የአፈፃፀም አደማስ እንዲሰፋ ተደርጓል፡፡

በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ለማፍራት ለ25 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ ሴክተሮች የተወታጡ ባለሙያዎች የስልጠናዉ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በአንድ መ/ቤት የኔትዎርክ አፒሊኬሺን ለመዘርጋት በታቀደዉ መሠረት በመምሪያችን የኔት ወርክ እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

የተገልጋዮችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት የተቋማትን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለዉ የሰዉ ሀብት ከማፍራት ረገድ በጥናት ላይ የተመሰረቱ ፣ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት እጅግ ወሳኝ የሆነዉን የሰለጠነ የሰዉ ሀይል በተፈለገዉ መጠን ለማፍራት አስፈላጊ የሆኑ ፣ የዕዉቀት፣ የክህሎትና ብቃት ማሳደጊያ የሚሆኑ የስራ አመራርና የለዉጥ ነክ አጫጭር ስልጠና እስከ ሀገር ዉስጥና የዉጭ አገር የረጂም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና ዕድሎችን በማስተባበር ተሠርቷል፡፡

-- በዚህ መሠረት በሀገር ዉስጥ የረዥም ጊዜ የደረጃ ማሻሻያ የትምህርት ዕድልን በተመለከተ:-

- የኢ.ሲ.ሰርቪስ ኮሌጅ ከአዋሳ ስራ አመራር ኢንስትቲዩት ጋር በተባበር በርቀት በ3 የትምህርት ዘርፎች/ በህግ፣ ማንጅሜንትና በአካዉንትንግ/ ከሰርቲፊኬት ወደ ዲፐሎማ ለማሸጋገር ለመንግስት ሠራተኞ የሚሰጠዉ የት/ዕድል ከዞናች 74 ሰራተኞ ተመልምለዉ ከተላኩ በኃላ 38 ሠራተኞች ተጣርተዉ በአርባ ምንጭ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ቱቶሪያል ማዕከል ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ክንዉን 51.65% ነዉ፡፡

- በ /ፊደራል ኤንድ ሎካል ገቨርንመንት ስቴዲስ/ በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ከዞናችን 5 ዕጩዎች ለፈተና ከቀረቡ በኃላ 1 ፈተናዉን በማለፍ በትምህርት ላይ ይገኛል፡፡

በ4 የትምህርት ዘርፎች /አርባን ፕላንንግ ሎው ፐቢልክ ፊናንሻል ስተዲስ ዲቨሎፐምንት ኢኮኖሚክስ / 38 ዕጩዎች ለፈተና ተመልምለዉ ሁሉም ፈተና ከተቀበሉ በኃላ ዉጤታቸዉ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

2/ ያጋጠሙ ችግሮች

1. የታቀዱ እቅዶችና ኘሮጀክቶችን ወደተግባሪ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ወረዳዎች በእቅዱ መሠረት ተወርውሮ ድጋፍ ለመስጠት የመኪና ውስንነትና ከዚህ ጋርም ተያይዞ ያለው የቀናት ውስንነት ድጋፋዊ ክትትሉን ተደራሽ በማድረጉ ላይ ተጽዕኖ ከማሳደሩ በላይ በቂ ድጋፉ እንዳይሰጥ ችግር መፍጠሩ ፣

2. በዞኑ የሚገኙ መምሪያዎች ሆነ ወረዳዎች የገቡትን ውል ከመ/ቤቱ ሠራተኞች ጋር ባለመወያየትና የጋራ ግንዛቤ ባለመጨበጥ የኘሮግራማቸው አካል ባለማድረጋቸው ለውጡ መሬት ከማውረድ አኳያ ችግር መፍጠሩ ፣

3. በየጊዜው ከሚተላለፉ መመሪያዎችና በጥናት ሰነዱ ከተቀመጠው አኳያ የሰው ኃይል አመዳደብ የተለያየ መልክ መያዘና በድጋፊዊ ክትትል ወቅት የአፈፃፀም ክፍተት መፍጠር ፣

4. ድጋፋዊ ክትትል ተደርጐ በሪፖርት ውሣኔ እንዲደረግባቸው የተቀመጡ ነጥቦች ላይ ስትሪንግ ኮሚቴው ያሳለፈው ውሣኔ ድጋፋዊ ክትትል ለሚያደርገው አለመቅረብ በቀጣዩም ለሚደረገው ድጋፋዊ ክትትል ተጽዕኖ ማሳደሩ ፣

5. የክልል የሥራ ሂደት የዞኑን ባለሙያች ለመደገፍና ለማብቃት እየተደረገ ያለው አፈፃፀም ደካማ ከመሆኑም ባሻገር የሥራ ሂደቱ ሌሎችን ተቋማት የማብቃት ሥራ የሚሠራ ሆኖ እያለ የተለያዩ ሥልጠናዎች ሲሰጡ የዚህ ሥራ ሂደት አባላት እንዲሣተፉ ባለመደረጉ ለአዳዲስ መረጃዎች እና አሠራሮች እንዳግዳ መሆንን ፈጥሯል ፣

6. መምሪያው የሚያከናውነው በአብዛኛው የአቅም ግንባታ ሥራዎች ማለትም በስብሰባ ፣ በፎረም ፣ በምክክር ጉባኤ በአጫጭር ስልጠናዎች ወዘተ አቅም መፈጠር ሲሆን ይህን ለመፈፀም የመሰብሰቢያ አዳራሽ የሌለውና በሌላ ሴክተር እጅ የሚገኙትም በተለያዩ ኘሮግራሞች ስለሚያዙ የኘሮግራሞች መፋለስ እና የእቅድ መውደቅ ማጋጠሙ ፣

7. የለውጡም ሆነ የሪፎርሙ ሥራ የኃላፊዎች ተቀዳሚ ኘሮጀክት እንደሆነ የተቀመጠ ቢሆንም ከተወሰኑ ኃላፊዎች በስተቀር ለድጋፍና ትብብር ያላቸው ተነሳሽነት አነስተኛ መሆን ፣

## 3/ ዓላማ

የመንግስት ተቋማትን የማስፈጸም አቅም በመገንባት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋገጥ በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ነው።

## 4/ ቁልፍ፣ አበይትና ንዑሳን የትኩረት መስኮች

### 4.1/ ቁልፍ የትኩረት መስክ፡-

የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በአዳዲስ አሰራር፣ አደረጃጀትና በበቃ የሰው ሃብት ልማትና አመራር በመታገዝ፤ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማሳለጥና በማቀላጠፍ ተቋማዊ ለውጥ / Organizational Transformation / እውን ማድረግና በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት

## 4.2/ አበይት የትኩረት መስኮች፡-

- በዞኑ የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት፣ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓትና የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት
- በሴክተሩ የሚከናወኑ ተግባራትን በመጽሔት፣ በራሪ ጽሑፎችና በልዩ ልዩ የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች በማጀብ ለህዝቡ ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስ ማድረግ
- የሴክተሩ አመራር በስርዓተ ጾታና በፀረ- ኤች አይ ቪ ኤድስ እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራና የመሪነት ሚና እንዲጫወት ማድረግ

5/ የአቅም ግንባታ ሴክተር ግቦች

5.1/ በቁልፍ የትኩረት መስክ

ግቦች

- የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ዳይመንዱን የተሟላ ለማድረግ ተጠንተው በሚወርዱ የጥናት ውጤቶች ከዞኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ አሰራር
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተተገበረ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/
- በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሰራር
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሰራር
- በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር

- በሁሉም የዞኑ የቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ አደር እንዲመራ ማድረግና አግምና ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ማስፋፋት፣
- በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ስርዓት
- በሁሉም ቀበሌያት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት
- በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ፣ወጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
- በክልሉ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት / ማህበረሰበ መረጃ ማዕከል፣ወረዳ ኔት፣እስኩል ኔት፣WAN, LAN…/
- 100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ
- 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈጻጸም ችግሮች ፣ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች
- በሰው ሃብት ልማትና ስልጠና አቅሙ የጎለበተ የዞን የወረዳና የከተማ አስተዳደር አመራርና ባለሙያ
- በዞኑ የሰው ሃብት ስራ አመራር በስራ ላይ የሚገኙትንና አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የተሰጠ ስልጠናና የምክር አገልግሎት

5.2/ በአበይት የትኩረት መስኮች
ግቦች

- ➢ በዞኑ የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት፣ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ
- ➢ በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ የሥርዓተ ፆታና ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ ስትራቴጂ
- ➢ በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ለህብረተሰቡና ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ መረጃዎች

6/ የሴክተሩ ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች

6.1/ በቁልፍ የትኩረት መስክ፦

- የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ዳይመንዱን የተሟላ ለማድረግ ተጠንተው በሚወርዱ የጥናት ውጤቶች ከዞኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ አሰራር
  - ከBPR ጋር የተጣጣመ የሽግግር ጊዜ የሥራ ምዘናና ደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት
  - በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ ሥርዓት
  - የማወዳደሪያ ዕውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት / charter and charter mark /
  - ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ የተዘረጋ ሥርዓት
  - የከፍተኛ አመራር ስርዓት / senior executives service /

- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተተገበረ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/

የሁለተኛ ዙር BPR ለሚተገብሩ ሴክተር መሥ/ቤት ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ለሙሉ ትግበራ የተሰጠ ስልጠና ፣

በሁሉም የመንግስት ተቋም የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ለመተግበር

የተደረገ ክትትልና ድጋፍ

- በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሰራር

የተዘጋጀና ታትሞ የተሠራጨ የውጤት ተኮር ማስፈጸሚያ ማኑዋል

በውጤት ተኮር የዕቅድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ የሰለጠኑ አመራሮችና ባለሙያዎች

በሁሉም ሴክተር መሥ/ቤቶች የተደረገ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ

- ○ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሰራር

- ➢ በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት
  - ከዞን እስከ ቀበሌ የተዘረጋና የተደራጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሰራር
  - በሁሉም ቀበሌ በፓኬጁ መሠረት የተቋቋመና ሥራ የጀመረ
    የኢንስፔክሽን ቡድን
  - በሁሉም ቀበሌ የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ወደ ሥራ ለማስገባት የተሰጠ ሥልጠና ፣
  - ለቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በእንስፔክሽን አሰራርና አደረጃጀት የተሰጠ ስልጠና፣
  - ➢ የእንስፔክሽን ውጤት፣ግብረ መልስና ሪፖርት
- ➢ በሁሉም የዞኑ የቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ አደር እንዲመራ ማድረግና አሣምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ማስፋፋት
  - ➢ በፓኬጅ ላይ በተገለፀው መስፈርት መሠረት በሞዴልነት የተመረጡ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች
  - ➢ የመሪነት ሚና መጫወት እንዲያስችላቸው የተሰጠ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ፣
  - ➢ የተመረጠ ሞዴል ግለሰብ መንደርና ቀበሌ ፣
  - ➢ የቀበሌ ምክር ቤት፣የቡዙሃን ማህበራት እንዲሁም የባህላዊ ተቋማት ተሳትፍን ለማጎልበት የተሰጠ ምክርና ድጋፍ
  - ➢ በዞንና ወረዳ ደረጃ የተጠናከረ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ
- ➢ በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ስርዓት
  1. የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምሮና ተቀናጅቶ ወደ ተግባር የሚወርዱበት የዕቅድ አዘገጃጀትና ሪፖርት አቀራረብ አሠራር፣
  2. በቀበሌ ደረጃ የተዘረጋ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት የመረጃና የጉዳይ አቀባበል አሠራር
  3. አራቱ የልማት ኮሚቴዎች በተቀናጀ ሁኔታ የሚሰሩበትን አሰራር በተጠናከረ መንገድ ማስቀጠል

4. በቀበሌና ወረዳ ደረጃ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ ለሥራ አስኪያጁና ለቀበሌ አመራር የተፈጠረ ግንዛቤ

- ➢ በሁሉም ቀበሌያት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት
- ➢ በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ፣ወጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል

በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት / ማህበረሰበ መረጃ ማዕከል፣ወረዳ ኔት፣እስኩል ኔት, LAN…/

- በሁሉም ሴክተሮች ለመሰራተዊ የአሰራር ስርዓት ጥናት / BPR / ለተገበሩ የስራ ሂደቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደረገ ድጋፍ
  1. በዞን በከተማና በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች የኔትወርክ ዝርጋታ ማከናወን
  2. በዞንና በወረዳና በከተማ የተበላሹ መሳሪያዎችን ጥገና ማከናወን የ ICT መሳሪያዎችን መጠገን
  3. በዞን በወረዳና በከተሞች አገልግሎት አሰጣጡን ሊያቀላጥፉ የሚችሉ የሶፍትዌርና የድረገጽ ስራዎችን መስራትና ማሰራት በተለይም በከተማ ማዘጋጃቤት ያለውን የመረጃ አያያዝና አሰራር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ማስቻል
  4. በሪፎርም ከተሞች ያለውን የግብር አሰባሰብ ስራ ሊያቀላጥፍ የሚችል ስርአት መዘርጋት
  5. አርሶአደሩ የገብያ መረጃና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስርዓት መፍጠር
  6. በዞንና ወረዳ ለሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች የሲስተም ዴቨሎፐመንት ሥራ ማከናወን
- የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራት የተሰጠ ስልጠና

በመሰረታዊ ኮምፒውተር አጠቃቀምና የተሰጠ ሥልጠና

በኢንተርኔትና ኢሜየል አጣቃቀም የተሰጠ ስልጠና

-ከዞን እስከ ወረዳ ያሉትን (ICT) መዋቅርን ማደራጀትና ለሌሎች ሴክተር

መስሪያ ቤቶችን ለማብቃት  የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍ

በዞንና በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ማከናወን

በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች በኢ.ኮ.ቴ ስራ ሂደት ለተመደቡ ፈፃሚዎች በጥናት ሠነዱ ላይ የተሰጠ ስልጠና

በገጠርና በከተማ የሚገኙ የማህበረሰቦች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ የጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል

የተቋቋሙ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከሎችን የማጠናከር የመደገፍና የክትትል ሥራ ማከናወን

በመንግስት ለተቋቋሙት የማህበረሰብ መረጃ ማዕከሎችን የአሰራር መመሪያ ማውጣት

- .100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላመረጃ ወቅቱን ጠብቀው እና በአግባቡ ተደራጅተው የተቀመጡ የውሣኔ መዛግብት ለተገልጋዮች የተሠጡ መረጃዎች

100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈጻጸም ችግሮች ፣ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች

ለቀረበ ቅሬታ  ተጣርቶ የተሠጠ ውሳኔ

ለቀረበ ቅሬታ በስፍራው በአካል ተገኝቶ የተጣራና የተሠጠ ውሣኔ

የተፈጸመ የቅሬታ ውሣኔ

በሰው ሀብት አመራር የአፈጻጸም ክፍተት መነሻ ለቀረበ  የይግባኝ ጉዳይ ውሣኔ መስጠት

በመደበኛ ስሚ ሂደት ተጣርቶ የተሠጠ ውሣኔ

በአካል ተገኝቶ ማስረጃ ማጣራት በተዘዋዋሪ ችሎት የተሠጠ የይግባኝ ውሣኔ

በሰው ሃብት ልማት በስልጠና አቅሙ የጎለበተ  የዞን የወረዳና የከተማ አስተዳደር አመራርና ባለሙያ እንዲሁም ለመንግስት ሠራተኞች በመንግስት ፖሊሲና በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ፅንሰ ሃሳብ ላይ የተሠጠ ስልጠና

በ BSC ለአመራርና ለባለሙያ የተሰጠ ሥልጠና

ምደባ ያላገኙና ተመልምለው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የገቡ ሠራተኞች

የሴክተሮችን/የተገልጋዮችን ፍላጎት መሠረት አድርጎ የተሰጠ ሥልጠና

ለሰው ሀብት ልማት፣ የለውጥ አስተባባሪና ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ባለሙያች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሰጠ ስልጠና

ለቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በመንግስት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች፣ በአመራር፣ በቀበሌ ስራ አስኪያጆች ተግባርና ኃላፊነት ላይ ስልጠና መስጠት፣

የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድሎችነ በማፈላለግ የተከናወነ የማስተባበር ሥራ

የተሰጡ ሥልጠናዎች በትክክል ስለመተግበራቸው የተደረገ ክትትልና ድጋፍ

.......በመንግስት ፖሊሲዎችና በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ፅንሰ ሃሳብ ላይ ለመንግስት ሰራተኞች የተሠጠ ሥልጠና

6.2/ በአበይት የትኩረት መስኮች

**በዞኑ የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት፣ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ**

የተዘጋጀ የ5 ዓመት የተቋም ስትራቴጂ ዕቅድ
የተዘጋጀ የቀጣይ ዓመት ዕቅድ
በየሴክተሩና በተዋረድ ያሉ የሰ/ሀ/ልማት ደጋፊ የሥራ ሂደቶችን በተቀናጀ መልኩ ለመምራት የተዘረጋ የዕቅድ የሪፖርት አቀራረብና የግንኙነት ሥርዓት
የተዘጋጀ የየሩብ ዓመት ሪፖርት

በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ የሥርዓተ ፆታና ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ ስትራቴጂ

በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ለህብረተሰቡና ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ መረጃዎች

የተዘጋጀ በራሪ ጽሑፍ

ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶች ለመሙላት የተደረጉ ጥናቶች

የተካሄደ የሥልጠና ፍላጐት ጥናት

# 7. የዓመታዊ ግቦች ውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ አመልካቾች

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች / Outcome indicators / | የፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| I. | ቁልፍ የትኩረት መስክ | የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በአዳዲስ አሰራር፣ አደረጃጀትና በበቃ የሰው ሃብት ልማትና አመራር በመታገዝ፤ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማሳለጥና በማቀላጠፍ ተቋማዊ ለውጥ /Organizational Transformation / እውን ማድረግና በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት | | |
| 1 | የሲቪል ሰረቪሲ ማሻሻያ ኘሮግራሞች የፍስማኘ እና የወአግኘ ቁልፍ የትኩረት መስክ | | | |
| 1.1 | የሲሰማኘ በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ ማዋል እንድያስችል በዙሉ የመንግሥት ተቋማት የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለወጥ ጥናት በመተግበር ተቋማዊ ለውጥ / /Organizational Transformation/ እንድመጣ ማድረግ | | | |
| 1.1.1 | የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በሁሉም የመንግስት ተቋማት ተቋማዊ መሠረት እንድይዝ ማስደረግ | የተሟላ የመሠረታዊ አሰራር ሂደት ጥናት ትግበራ<br>የተፋጠነ አገልግሎት አሰጣጥ<br>የተሻሻሉ አሰራሮች | ቀልጣፋ አገልገሎት አሰጣጥና የተገልጋዮች እርካታ<br>ውጤታማ የዕቅድ አፈፃፀም | የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማረጋገጥ |
| 1.1.2 | በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተተገበሩ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ ሥርዓት የመዘርጋት / BSC / | ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ምዘና ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት<br>የተፋጠነ አገልግሎት አሰጣጥና የተገልጋዮች እርካታ | ፍትሃዊና ቀልጣፋ የሕግ አሰራር<br>ተደራሽና ቀልጣፋ አገልግሎት | |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች / Outcome indicators / | የፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| 1.2 | የመልካም አስተዳደር ፖኬጆችን በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጉ ሥርዓቶችና እንደ ሥርዓት ሥራ ላይ እንድውል ማድረግና መሬት ማስረገጥ | | | |
| 1.2.1 | ዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌና የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ሥርዓት | ብቃት ያለው የገጠር ልማት ዕቅድ አፈፃፀም<br>የተቀናጀ አሰራር<br>የሕ/ቡ ጥያቄ ቶሎ ምላሽ ማግኘት | በቀበሌ ደረጃ የተጠናከረ አሰራር መዘርጋት<br>የቀበሌ የልማት እንቅስቃሴ ግልጽና ውጤታማ መሆን<br>የልማት ሰራን ማፋጠን | በቀበሌ ደረጃ የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 1.2.2 | ሕ/ቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሣተፍና አሣምኖ ማሠራትን ባህል ለማዳበረ ግልጽና ተጠያቅነት ያለው አሰራርና ሞዴል የመጠቀም የተዘረጋ ሥርዓት | ብቃት ያለው የገጠር ልማት ዕቅድ አፈፃፀም<br>ሕ/ቡን ተሣተፎ መጨመር<br>የሕ/ቡን ጥያቄ ቶሎ ምላሽ ማገኘት<br>የሕ/ቡን እንግልት መቀነስ | አ/አደሩ በግልና በጋራ ሥራ በንቃት መሣተፍ<br>በቀበሌው የማሕበራዊ አገልግሎት መጠናከር | የግብርና ምርት መጨመር<br>የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማምጣተ<br>የአ/አደረ ገቢ መጨመር |
| 1.3 | በዞኑ የፍትሕ ሥርዓት ለማሻሻልና ከመሠረቱ ለመለወጥ የተወጠኑ ሥራዎችን በማጠናከር የፍትሕ አካላቱን ተደራሽነት፣ ቀልጣፋነትና ውጤታማነተ ማረጋገጥ ፤ | | | |
| 1.3.1 | በዞኑ የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራምን ስኬታማነትና ውጤታማ ለማድረግ የፍትሕ | አቅማቸውን የተገባ የሕግ ባለሙያዎች | ፍትሀዊና ቀልጣፋ አሰራር ተደራሽና ቀልጣፋ | የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች / Outcome indicators / | የፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| | አካላትን ማብቃት | | አገልግሎት | |
| 1.3.2 | የሕ/ቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ ፈጣንና ፍትሕዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትሕ አካላት ጋር የበለጠ ቅንጅት እንድኖር የተዘረጋ ሥርዓት | በቀበሌ ደረጃ የተቋቋሙ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ አደረጃጀት | ፍትሀዊና ቀልጣፋ የሕግ አሰራር ተደራሽና ቀልጣፋ አገልግሎት | የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 2 | የሲሰማኘ የወአግኘ አበይት ትኩረት መስክ | | | |
| 2.1 | የሲሰማኘ በዞኑና በሁሉም ወረዳዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ክትትል በማካሄድና ቴክኒካል ድጋፍ በመስጠት የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ ማድረግና የሕዝበ አገልጋይነት ስሜት ሠራተኛው ዘነድ ግንዛቤ እንድፈጠር ማድረግ | | | |
| 2.1.1 | የአገልገሎት አሰጣጥ አንዱ አካል የሆነውን የቅሬታ ማስተናገኛ ሥርዓት በተጠናከረ መልኩ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ለማሳለጥ አገልገሎተ አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ እንድሆነ የተዘረጋው ሥርዓት | በአገልግሎት አሰጣጥ ድጋፍ የተደረገላቸው የመንግስት ተቋማት | ቀልጣፋ የአገልገሎት አሰጣጥና የተገልጋዮት እርካታ ውጤታማ የዕቅድ አፈፃፀም | የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 2.1.2 | በዞኑ በስትራቴጅክ ዕቅድ አመራር በዓመታዊ ዕቅድና ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ አሰራር ስርዓት በማስተሳሰረ በሁሉም የመንግስት | በስትራቴጅክ ዕቅድ ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ ስልጠና የወሰዱ ሠራተኞች ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ተግባራዊ ያደረጉ የመንግስት | ቀልጣፋ አገልገሎት አሰጣጥና የተገልጋዮተ እረካታ | የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች / Outcome indicators / | የፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| | ተቋማት እንደ ሥርዓት መትከል | ተቋማት | ውጤታማ የዕቅድ አፈፃፀም | |
| 2.2 | የወረዳና የቀበሌን ያልተማከለ አስተዳደር ፖሊስ ለማጠናከር ልዩ ልዩ ተቋማት ጥናቶችን ለማካሄድ ግብአት መስጠትና የወረዳን የማስፈጎም አቅም ለማጉልበት ኘሮጀክቶችን መተግበር | | | |
| 2.2.1 | በየደረጃው ባለ በሁሉም የመንግስት ተቋማትተያልተማከለ አስተዳደረር ስርዓት በተማላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የተጠኑና የሚጠኑ የጥናት ውጤቶችን መሬት በማስረገጥ እንደ ሥርዓት መዘረጋት | በሁሉም ሴክተሮች የተተገበሩ የጥናት ውጤቶች | የተዘረጋ ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት | የተፋጠነ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 3 | በወረዳ ደረጃ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሚያስችል የተፋጠነ አቅም | አቀም የተገነባላቸው ወረዳ ብዛት | የተዘረጋ ቀልጣፋ አሰራር | |
| 4 | የተቋሙን አገልግሎተ አሰጣጥ የተለየዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሕ/ቡ መረጃ ማሰራጨት | 5. በሚዲያ የተሰራጨ መረጃ<br>6. በብሮሸር የተሰራጨ መረጃ | የተገልጋዮች እርካታ | የተፋጠነ ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 5 | በክልሉ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት / ማህበረሰበ መረጃ ማዕከል፣ወረዳ ኔት፣እስኩል ኔት, LAN…/ | | | |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች / Outcome indicators / | የፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| 6 | 100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ | | | |
| 7 | 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈጻጸም ችግሮች ፣ ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች | | | |
| 8 | በሰው ሃብት ልማትና ስልጠና አቅሙ የጎለበተ የዞን የወረዳና የከተማ አስተዳደር አመራርና ባለሙያ | | | |
| 9 | ሰው ሃብት ስራ አመራር የሚዘረጉትን ነባርና አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የተሰጠ ስልጠናና የምክር አገልግሎት | | | |
| 10 | በዞኑ የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት፣ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ | | | |
| 11 | በሴክተሩ የተጠናከረ የስርአት የታየ ኤች አይ ቪ ኤድስ ማይን ስትሪንግ ስርአት | የአመለካከት ለውጥ ያመጡ ሠራተኞች | የተለወጠ አመለካከት ያለው ሠራተኛ | ጤናማ ዜጋና የተ ታዋፅኦ የተረጋገጠበት ልማት |

# የድርጊት መረሐ ግብር

| ተ.ቁ | የሚጠበቁ ውጤቶችን ዝርዝር ተግባራት | መለኪያ | መጠን | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | የሚያስፈልግ በጀት | ፈጻሚ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ❖ የሲሰማኘ በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ ማዋል እንዲያስችል በዞኑ የመንግስት ተቋማት የመሠረታዊ የሥራ ሂደተ ለውጥ ጥናት በመተግበር ተቋማዊ ለውጥ /Organizational Transformation/ እነዲመጣ ማድረግ | | | | | | | | | |
| 1.1 | የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በሁሉም የመንግስት ተቋማት ተቋማዊ መሠረት እንድይዘ ማድረግ | | | | | | | | | |
| | በትግበራ ወቅት ድጋፍና ክትትል ማድረግ | በዙር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | የለ/ፐ/ | |
| | በስትሪንግ ኮሚቴ በየወሩ መገምገምና አቀጣጫ ማሰቀመጥ | በዙር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | የለ/ፐ/ | |
| | ለወረዳዎች ድጋፍ መስጠት | በዙር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |
| 1.2 | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት አተገባበር ለሚሰጠው ስልጠና ማመቻቸት | | | | | | | | | |
| | ለሃያ ሴክተር መ/ቤቶች /BPR/ ዙሪያ በሚሰጠው ስልጠና ክትትል ድጋፍ ማድረግ | በዙር | 3 | 1 | 1 | 1 | - | | የለ/ፐ/ | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **1.3** | **የመሠረታዊ የሥራ ሂደተ ለውጥ ወደ ሙለ ትግበራ ለሚገቡ የተሰጠ ተክኒካል ድጋፍና ግምገማ** | | | | | | | | | |
| | **በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ለሙሉ ትግበራ ተክኒካል ድጋፍ መስጠት** | **በቁጥር** | **12** | **3** | **3** | **3** | **3** | | **የለ/ፐ/** | |
| **2** | ❖ **በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተተገበሩ ሚዛናዊየውጤት ተኮር ዕቅድ ሥርዓት የመዘርጋት** / BSC / | | | | | | | | | |
| **2.1** | **የምዛናዊ ውጤት ተኮር አፈፃፀም ዙሪያ የሚሰጠው ሰልጠና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ** | **በዙር** | **2** | | 1 | 1 | | | **የለ/ፐ/** | |
| | /BSC/ **አተገባበረ ማጠናቀርናየ አፈፃፀሙን በስትርኒገ ኮሚቴ መገምገም** | **በዙር** | **12** | **1** | **1** | **1** | **1** | | **የለ/ፐ/** | |
| **3** | ❖ **የመልካም አስተዳደር ፖኬጆች በወረዳና ቀበሌ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጉ እንዳብ እንደ ስርአት ሥራ ላይ እንድውል ማድረግ**<br>❖ **ለሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደረ 9ኬጁ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የእነስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ሥርአት** | | | | | | | | | |
| **3.1** | **ከወረዳ እስከ ቀበለ የተቋቋመ የኢንስፔክሽን ቡድኖችን መደገፍ** | **በቁጥር** | **456 ቀበሌ ያት በ4ዙ ር** | **1** | 1 | 1 | 1 | | **የለ/ፐ/** | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **3.2** | የሞዴል አ/አደር መምረጫ መስፈርት ማሰራጨት | በቁጥር | **1** | **1** | | | | | የለ/ፐ/ | |
| | የተመረጡ ቀበሌያት መንደሮችና ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች የቀበሌ ልማትን መደገፍሣ ክትትል ማድረ | በዙር | **2** | | 1 | 1 | | | የለ/ፐ/ | |
| **3.3** | ❖ በቀበሌ ደረጃ የተዘረጋ አሰራር ሥርአት ማጠናከር እንድሁም የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአትና የመረጃና ጉዳይ ተቀባይ አሰራር ሥርአት መዘርጋት | | | | | | | | | |
| | በቀበሌ ደረጃ ለተቋቋመ የመረጃና ጉዳይ ተቀባይ ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | **456 ቀበሌ** 15 **ወረዳ** | **1** | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |
| | የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምሮና ተደረጅቶ ስራ ላይ የሚውልበት መመሪያ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል | በዙር | **12** | **3** | 3 | 3 | 3 | | የለ/ፐ/ | |
| **4** | በፍሰማኘ የሕ/ቡን ሰላምና ፀጥታን ለማሰጠበቅና ፈጣነ ፍትሀዊ አገልግሎተ ለመሰጠት ከፍተሕ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ሥረአት | | | | | | | | | |
| **4.1** | በፍትሕ ሥርአት የወጡ ሕጐችና መመሪያዎችን ማሰራጨት<br><br>የህትመት ውጤቶችን ለተጠቃሚው በወቅቱ ማሰራጨት | በዙር | **3** | **1** | | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |
| **4.2** | በሁሉም የከተማና የገጠረ ቀበሌያት የኮሚኒት ፖሊስንግ እንድጠናከር የተዘረጋ ሥርአት<br>በሁሉም ወረዳዎተ ክትትል ማድረግ | በዙር | **4** | **1** | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የአገልግሎተ አሰጣጥ ፖሊሲ በተጠናከረ መልኩ በሁሉም የመንግስት ተቋማት በማሳለጥ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋና ውጤታማ እነድሆን የተዘረጋ ሥርአት | | | | | | | | | |
| 5.1 | በሁሉም የመንግስት ተቋማት የ Quik wine ሥራዎች አጠናከሮ መቀጠል | በቁጥር | **267** | **66.75** | **66.75** | **66.75** | **66.75** | | የለ/ፐ/ | |
| 5.2 | በመንግስት ፖሊሲ፣ ስትራቴጅና በአዳድስ ኘሮጀቶች ላይ ስልጠና እንድሰጥ ማመቻቸት | በዙር | **4** | **1** | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |
| 5.3 | በረካታ ተገልጋዮች ካሉባቸው የመንግስት ተቋማት የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርአተ መዘርጋት | በቁጥር | **60** | **15** | 15 | 15 | 15 | | የለ/ፐ/ | |
| 5.4 | የሕዝብ አስተያየት ማወቂያ ጥናት በማካሄድ ግባት ማዘጋጀት | በቁጥር | | | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |
| 6 | ከዞን እስከ ወረዳ በስትራቴጅክ ዕቅድ አመራር በዓመታዊ ዕቅድ በBSC /በሚዛናዊ ውጠት ተኮር ዕቅድ አሰራር ሥርአት በማስተሳሰረ በሁሉም የመንግስት ተቋማት እንደ ሥርአት መትከል | | | | | | | | | |
| 6.1 | በ100% በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተቀናጀት ዕቅድ መዘርጋት<br>በዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | በቁጥር | **267** | **66.75** | **66.75** | **66.75** | **66.75** | | የለ/ፐ/ | |
| 7 | በየደረጃው ባሉ በሁሉም የመንግስት ያልተማከለ አስተዳደር ሥርአት በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር አዳድስ ጥናት ማድረግና የተጠሃቀቁ የጥናተ ውጤቶችን ተግባራዊ ማድረግ | | | | | | | | | |
| 7.1 | የወረዳ የሕግ ማሣተፍ ያልተማከለ አሰራር ፖሊሲ የተገበረ ወረዳ<br>የተዘጋጁ ሥርአቶች ሥራ ላይ እንድውሉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በዙር | **4** | **1** | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፐ/ | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | |
| 8 | በሴክተሩ የተጠናከረ የሥርአተ ፆታና ኤች አይ ቪ ኤድስ ማንስትሪንግ ሥረአት | | | | | | | | | |
| 8.1 | በሴክተሩ የተካሄደ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች በስርአተ ፆታ ላይ የመጡ ለውጥ የዳሰሳ ጥናት ግብአት ማሰባሰብ<br><br>ለጥናቱ ግብአት ማሰባሰብ | በቁጥር | 1 | | | 1 | | | የለ/ፕ/ | |
| 8.2 | በሥርአተ ፆታ ላይ በአሰራር ለ250 ለአቅም ግንባታ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚሰጥ<br>በስልጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸት | በዙር | 1 | | 1 | | | | የለ/ፕ/ | |
| 8.3 | በመነገስት መ/ቤቶች በስራ አመራር፣ በት/ት ስልጠና የሴቶችን ተሣተፎ ለማሳደግ የተዘረጋ<br><br>የተዘጋጁ መመሪያዎች ማሰራጨትና ማስተዋወቅ | በቁጥር | 1 | | | 1 | | | የለ/ፕ/ | |
| 8.4 | በሥርአቴ ፆታና ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከል በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል | በዙር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፕ/ | |
| 9 | የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ በተለያዩ የበዙሃን መገናኛ ዜዴዎች በሕ/ቡ መረጃ ማሰራጨት | | | | | | | | | |
| 9.1 | 8 በሮሸሮችን አዘጋጅቶ ማሰራጨት | በቁጥር | 6 | | 2 | 2 | 2 | | የለ/ፕ/ | |
| 9.2 | አንድ መጽሄት ማዘጋጀት | በቁጥር | 1 | | | | 1 | | የለ/ፕ/ | |
| 9.3 | 4 ጊዜ የሚዲያ ሽፋን መስጠት | በጊዜ | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | የለ/ፕ/ | |

## 9. አዎንታዊና አሉታዊ ታሳቢዎች

### 9.1 አዎንታዊ ታሳቢዎች

- በ 2002 በጀት ዓመት ጀምሮ /PSCAP TWO/ ፒስካፕ ለቀጣይ አምስት አመት የሚቀጥል መሆኑ
- የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻልና የአመለካከት ለውጥ መኖር
- የሠራተኞች ግንዛቤ መዳበርና በግቦች ላይ የጋራ መግባባት መፈጠር
- የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ የመጀመሪያ ዙር በተሳካ መልኩ ወደ ሙሉ ትግበራ መገባቱ
- በአለም ባንክ በኩል ያሉ አሰራሮች መሻሻሉ
- የተጠያቂነትና የግልጸኝነት አሰራር እየሰፈነ መምጣቱ

### 9.2 አሉታዊ ታሳቢዎች

- ብድርና ዕርዳታ በጀት መዘግየትና የዶላር ምንዛሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ መምጣቱ
- የሴክተሩ የበመደበኛ በጀት ማነስ
- ተሽከርካሪ ተሟልቶ አለመገኘት
- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ በደረጃው የሚገኙ አመራሮች ግንዛቤ ውሱንነትና ቁርጠኝነት አለመኖር
- የአመራሩ አካላትና ባለሙያዎች በየጊዜው መቀያየርና መልቀቅ
- የሰው ሀይል በሚፈለገው መጠን አለመሟላት
- የተጠናከረ የሕዝብ ግብኙነትና የመረጃ ሥርዓት ያለመዳበር
- የፒስካፕ በጀት አጠቃቀም በዕቅድ ላይ አለመመስረትና በደራሽ ሥራ ላይ ማተኮር

## 10. የክትትል፣ሪፖርት እና ግምገማ ስርዓት

በአወንታዊ ታሳቢነት ተለይተው የተቀመጡ ዋና ዋና ጉዳዩች እንደተጠበቁ ሆነ ሴክተሩ ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ ለመፈጸምና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ብሎም ተልዕኮዉን ለመወጣት በሚያስችል ሁኔታ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ነድፎ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

## 10.1 የክትትልና ሪፖርት ስርዓት

የክትትል ተግባር በቀጣይነት የዕቅዱ አፈጻጸም በምን ያህል መጠን፣ በምን ያህል የጊዜ ፍጥነት፣ በምን የጥራት ደረጃና በምን ያህል ወጪ ወይም በአጠቃላይ ዕቅዱ ሊተገበርበት በታሰበባቸው መስፈርቶችና የውጤት አመለካቾች (output and outcome indicators) መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ከተገቢው ምንጭ መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚተነተንበት ሂደት ነው፡፡ በተጨማሪም በክትትሉ ሂደት ተለይተው የወጡ ድክመቶችና ጠንካራ ጎኖች በቀጣዩ የዕቅድ ክንውን ወቅት ግብዓት በመሆን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችልና ግምገማ በሚካሄድበት ወቅት በመረጃነት የሚያገለግል ነው፡፡

የክትትል ስራ በሥራ ሂደት አስተሳሰብ በተቀረጸው መሰረት ሥራዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት እየተከናወኑ ስለመሆናቸው በስራ ሂደቱ ባለቤት ቢያንስ በየሁለት ሳምንቱ ክትትል ሊካሄድ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ የምንከተላቸው የክትትል ስርዓቶች/ስልቶች፡-

1. ወቅታዊ ሪፖርቶችና መረጃዎችን በመጠቀም ክትትል ማድረግ፣
2. የሚከናወኑትን የትኩረት መስኮች በየጊዜዉ ቴክኒካል ድጋፍ በመስጠት
3. አጠቃላይ ክልላዊ የአቅም ግንባታ ሴክተር የምክክር ጉባዔ በስድስት ወር
4. የዕቅድ አፈጻጸሞች ክትትል ሲደረግ የውጤት አመልካቾች መሰረት መሆን

በአጠቃላይ ከሚቀርቡ ሪፖርቶችና ከሚሰበሰቡ የተገልጋይና የሠራተኛ አስተያየቶች መነሻ ሰፊና ተገቢ መድረኮችን በማዘጋጀት መወያየትና በስራው ሂደት የተከሰቱ ቁልፍ ችግሮችንና የችግሮችን መንስኤ በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችን ማውጣትና ለቀጣዩ የዕቅድ አፈጻጸም ያላቸውን ጠቀሜታ መወሰንና መመዝገብ ያሻል፡፡ በዕቅዱ አፈጻጸም በሚካሄዱ የክትትልና ግማገማ መሰረት ወቅታዊና ትክክለኛ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ አካላት ለሚመለከታቸው አካላት በወር፣ በሶስት፣ በስድስትና በዓመት ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ሪፖርቱ የደረሳቸው ክፍሎችም ለተካሄደው አፈጻጸም ሪፖርትና መረጃ ግብረመልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

## 10.2 የግምገማ ስርዓት

የግምገማው ስርዓት ውጤትንና ስኬትን መለካት የሚያስችል የጊዜ ስፋት መከናወን ስለሚገባው ቢያንስ በየሶስት ወር አንድ ጊዜ መከናወን ያለበት ነው፡፡ ግምገማ በዕቅድ ዉስጥ በተቀመጠዉ ጊዜ ገደብ በክትትል የተገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ይህም ዕቅዱን በጊዜ ገደብ ለመስራት ከታቀደው ምን ያህሉን በምን ያህል ወጪና በምን ዓይነት ጥራት እንደተተገበረ ካጋጠሙት መሰናክሎችና መልካም ገጠመኞች አንጻር የሚገመገምበት ነው፡፡

በአጠቃላይ የክትትልና የግምገማው ስርዓት በተከታታይ የሚከናወን ሆኖ የሚመለከታቸውን አከላት በተሟላ ሁኔታ ያሳተፈና የመረጃው አሰባሰብ ከተለያዩ አከላት ተወስዶ የተነጻጸረና በተገቢው ሁኔታ የተጣራ መሆን ይገባዋል፡፡ በተጨማሪ ክትትሉም ሆነ ግምገማው ሲካሄድ ከተዘረዘሩት የውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ/ለውጥ አመልካቾች (output, outcome and impact indicators) ለግቡ መፈጸም ከሚያደርጉት አስተዋጽዖ አንጻር መሆን ይኖርበታል፡፡